# እውነተኛና ዘላቂ ግንባታ

andualem19@yahoo.com

*አሁን አሁን ደግሞ ከገዢው ፓርቲ ሰዎች ጋርም ይሁን ባምሳላቸው ከሰሩዋቸው ደጋፊዎቻቸው ጋር ላንድ አፍታም ቢሆን ትነሽ ንግግር ሲጅመር ጭራሽ ደንቆሮ ይመስል አላግባባ ያለ አዲስ ችግር ከተፈጠረ ሰነበት አለ፤ ግንባታ፣ግንባታ፣ግድብ፣ግድብ....ወዘተ የሚለው አሰልቺ ዘፈን ነው::ይህ አባባሌ ምናልባት አሁን ሁሉንም ነገር አጣመው ምውሰድ ለሚችሉበት የገዢው ፓርቲ አባላት ወይም የተሳሳቱ ደጋፊዎች ጣት የሚያስቀስርብኝ ኢነደሚሆን አምናልሁ::መገንዘብ ያልቻሉት ትልቅ ነገር ግን በጭራሽ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ወይም በሰው ደረጃ ራሱ ሰው ያልሆነ ሰው በቀር አንድን መሰረተ ልማት የሚጠላ ይኖራል በሎ ማመን በጣም ከባድ ነው ያውም ለዘመናት ሲናፈቅ የቆየው ትልቁ አባይ ቀርቶ።*

*ትለቁ ጥያቄ ሆኖ መልሰ የጠፋለት ግን ዓባይን የሚያክል ትልቅ ግድብ፣የባቡር ሃዲድን የሚያክል ትልቅ እና እሰየሁ የሚያስብል ሰራ ለመሰራት የቆረጠ ሰርአት ወይም መንግሰት በጣም ትንሽ እና መሰረታዊ የሆነውን የሰው መበት/ነጻነት ማክበር ምነው ይሄን ያህል ተቸገረ?የትኛውስ ነው ብዙ ውጪና ድካም የሚጠይቀው?ይሄ ሁሉ ድካምና ሩጫ ለህዝብ ነው ከተባለ በቅድሚያ ያ የሚደከምለት ህዝብ፣ያ የልማቱ ተጠቃሚ ይሆናል የሚባልለት ህዝብ ደህንነቱ፣ሰላሙ፣በልቶ ማደሩ፣ ቢያንስ እንደ ሰው መኖሩ መታወቅ የለበትም ወይ?በቅድሚያ አንድ አካል በሰላም መኖሩ ሲታወቅ አይደለም ወይ ለዛ አካል ሌላ አንድ ተጨማሪ ነገር ያስፈልገዋል የሚባለው?ጤናው የተስተካከለና ሁኔታዎች በወጉ የተሟሉለት ቡድን ሳይኖር የመጫወቻ ሜዳ ብቻውን መገንባቱ ከፈረሱ ጋሪው አይደለም ወይ?እውነት እንነጋገር ከተባለ “እመራሀለው ወይም ቆሜልሀለው”ከሚባልለት ህዝብ ጋር ቀላል የሆነችዋን ሰላም/ፍቅር መገንባት ከሌላው አድካሚና “የእርዳታ ያለህ እየተበለ“በዓለም ዙሪያ ከሚያስጨህ ስራ ጋር እንዴት ይሆን የሚነጻጸረው!?ዘመናትን አስቆጥረው እስከ አሁን በመዝለቅ የኢትዮጵያ ኩራት የሆኑት የአክሱም ሃውልት፣የላሊበላ፣የጎንደር፣የሃረር፣የጅማ...ወዘተ የግንባታ ውጤቶች እኮ“ የአይ ኤም ኤፍ“እርዳታ ሳያስፈልጋቸው በህዝብ ፍቅር እና ጽኑ አንድነት በቀላሉ የተገነቡ በመሆናቸው እነሆ ለዘመናት ዘልቀው ዛሬም ውበት ሆነውናል::ህዝብ በፍቅር ሲያዝና ቀላል የሆነው መሰረታዊ መብቱ ሲጠበቅ በእንብርክኩም ሄዶ ቢሆን የተባለውን ለማድረግ አያመነታም፤ያውም ኢትዮጵያዊ!!!ለዚህም ነው በፍቀርና በጽኑ አንድነት ላይ የተመሰረተ ግንባታ ዘላቂነቱ ለጥያቄ የማይቀርበው።ገንቢውም ጠባቂውም ህዝብ ነው።በገንዘብ/እርዳታ ላይ የተመሰረተው ግን ገንዘቡ ሲቆም ይቆማል ወይም ገንዘቡ በሚያመጣው መዘዝ ይናጋል።ስለዚህ መሰረታዊ እውነት መናገር ወይም ማሳሰብ በፍጹም ጸረ ልማት አያስብልም!”የምን አየኑ-ደረቅ መልሶ....”እንደሚባለው ካልሆነ በቀር!።*

*“መጽደቁ ቀርቶ በቀጡ በኮነነኝ” እንደሚባለው የሚያሳዝነው ግን የበፊት ቁስሎች ሳይሽሩ፤ ለዚቾው ለምናወራት ትንሽ ግን መሠረታዊ ሰለሆነች የሰው ልጅ መብት በመጨሃቸው ዘብጥያ የተወረወሩ ሳይወጡ፤በደል የፈጸሙ(ለይስሙላ እንኳ) ለፍርድ ሳይቀርቡ፤እስቲ ዛሬም በሰላም እንሞክር ብለው በገዛ ሃገራቸው ለመሰባሰብ የሚሞክሩ ድርጅቶችና የፖለቲካ ፓረቲዎች አዳራሽ ሲከለከሉና በደህንነት ሰዎች ተዋክበው ለእሥር እና ለዱላ ሲዳረጉ፤እምነት አልባ ተሁኖ ከ ቄሱም ከ ሼኩም ሳይሰማሙ አሁን ደግሞ “ባእንቅርት ላይ....”እንዲሉ ዜጎችን ማፈናቀል እንደ አዲስ ሰልት ተግባራዊ እየሆነ ነው። “ማፈናቀል”ከሚለው ይልቅ “ማተራመስ”ወይም ”ፈፅሞ እንዳይሰክን አርጎ መበጥበጥ”በሚለው ቢተካ ይቀላል ምክንያቱም ይኸው ተመለሱም ተብሎ ተረጋግቶ የመኖራቸው ጉዳይ አደጋ ላይ ወድቋል፤አብረው ከኖሩት ህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆነው ሰለወደፊቱ ምንም ዋሰትና የላቸውም።እንዲህ ነው እነግዲህ “የህዝብን በጋራ ተፈቃቅሮና ተከባብሮ፣አንድነቱን ጠብቆ እንዲኖር የማድረግ ራዕይ!!!!”ወይሰ እኔ/እኛ አልገባንም?!*

*ብዙ ብዙ የተባለላቸዉ የሟቹ ጠ/ሚር ራዕይስ ይሄ ነበረ ወይ?ወይስ ሰማቸዉ ከመቃብር በላይ በጥሩ እንዳይነሳ ራዕያቸዉን ማበላሸት ተይዟል!?ማሽሟጠጤ አይደለም እመኑኝ፤ግራ ገባኝ እኮ ምን ለድረግ!የሚወራዉና የሚሠራዉ አንድ አልሆን ሲለኝ!አሁን እነግዲህ አጭር እና ግልጽ ነገር አለ፤ ይኸዉም የጠፋዉን ሁሉ በማረም፣ከህዝብ ጋር በመታረቅ፤ይቅር ለመባባል በመዘጋጀት....ወዘተ "እሰየሁ!! ለካስ የሄ ነበር ራዕዩ!!"ብለን እነድናመሰግን መድረግ ይህ ካልሆነና አሁን በተያዘዉ መንገድ ለመጓዝ ከሆነ ግን "እናንተንም በተቀደደዉ ቦይ ይዟችሁ ይሂድ ብለን እንጸልይ" "የማሞን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም!!"ማለት ግን ብልህነት ከመሆኑም በላይ ለልጅ ልጅም ዕዳ አለማቆየት ነዉ!!!እንዲህ አይነቱን ክፉ ራዕይ ለማሳካት ከሆነ ግን ጊዜ ይፍጅ እንጂ እንኳን መልዐክ ሰይጣንም ፈጽሞ አያሳካዉም!እንኳን ኢትዮጵያን የመሰለ ያአምላክ ጥበቃ የበዛላት ሀገር ቀርቶ!!*

*ይልቅ ጊዜ ሳየረፍድ ወደ ልቦናችን እንድንመለስ ጥረት ማድረግ ነዉ።የቋጠርናትንም በወጉ እንድንበላ ሰላሟ የተጠበቀ፣የዜጎቿ ነጻነት የተረጋገጠባት፣ጥሎ ለመሰደድ ሳይሆን ቸኩሎ በናፍቆት የሚሮጥባት፣በቀንም ሆነ በምሽት ያለ ፍርሃት የሚኬድባት፣አንድነቷ የተረጋገጠ የጋራ ሀገር እንድትኖረን ቆም ብሎ ማሰብ ግድ ይላል።መንግስት አስተዳድርሃለዉ የሚለዉን ዜጋ ነጻነት እና መሰረታዊ መብት ማክበር፤ዜጎችም መንግስት የኔ ነዉ ብለዉ በነጻነት እና በኩራት መንቀሳቀሳቸዉ ለየትኛዉም ዓይነት ዘላቂ እና እዉነተኛ ግንባታ የማይናጋ መሠረት ነዉ።ይህ ሳይሆን የሚሮጥለት የድንጋይና የብረት ግንባታ ግን አንድ ድግሥ እስከሚያልፍ ከሚደረግ ጊዜያዊ ያዳራሽ ጌጥነት አያልፍም።*

***ልቦና ይስጠን!!እግዚአብሔር ኢትዮጵያንም ህዝቧንም የባርክ!!!***

*አንዱዓለም(ከስዊስ)*

*Andualem19@yahoo.com(Switzerland)*